የዕጩ ምዝገባ መልመጃ፣ ሁኔታ **3**

ሁኔታ፡ በሀረሪ ክልል ለህዝብ ተወካዮች ምክርቤት መቀመጫ መወዳደር የሚፈልግ XYZ የተባለ ግለሰብ ለምርጫ ክልሉ ጽ/ቤት ማመልከቻ አቀረበ። ማመልከቻውን በጥንቃቄ ሞልቶ እና ተፈላጊ ማስረጃዎችን አያይዞ ያቀረበ ቢሆንም የምርጫ አስፈጻሚው ማመልከቻውን ውድቅ አደረገበት። ዕጩው በውጪ ሀገር ለብዙ አመታት ቆይቶ በቅርብ ወራት ወደ ምርጫ ክልሉ የተመለሰ ነበር። የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው ላቀረበው የመረጃ ጥያቄ የመርጫ አስፈጻሚው በሰጠው መልስ ማመልከቻውን ውድቅ ያደረገው ዕጩው የነዋሪነት መስፈርትን እና የግልዕጩ ሆኖ ለመቅረብ የሚያስፈልገውን የ 2500 የድጋፍ ፊርማ ስላልተሟላ እንደሆነ አብራርቷል። የምርጫ ክልሉ ቀሬታ ሰሚ ኮሚቴ በምርጫ አስፈጻሚው ውሳኔ በመስማማት ቅሬታውን ውድቅ አድርጎታል። XYZ የተባለው ግለሰብ በምርጫ ክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠወው ውሳኔ ላይ ያለውን ቅሬታ ለክልሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ያቀረበ ሲሆን በውጪ አገር የኢትዮጲያ ኢምባሲ ሰራተኛ የነበረ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አያይዟል። የክልሉ ቀሬታ ሰሚ ኮሚቴ በህጉ ላይ ለኢትዮጲያ መንግስት ሰራተኞች የነዋሪነት መስፈርትን የሚያስቀር ልዩ ሁኔታ ያልተቀመጠ መሆኑን በመግለጽ ቅሬታውን ውድቅ አድርጎታል። ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይፈልጋል።

ጥያቄ 1. ቅሬታውን ለመስማት ሥልጣን ያለው ማነው? የትኛው ፍርድ ቤት? ( ወይም ሥልጣኑ አሁንም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ነው?)

ጥያቄ 2. ቅሬታ አቅራቢው መቼ እና የት ቅሬታውን ያቅርብ?

ጥያቄ 3. ጉዳዩ መቼ ውሳኔ ያግኝ?

ጥያቄ 4. ክሱን ለማስረዳት ምን አይነት ማስረጃ ሊቀርብ ይችላል?

ጥያቄ 5. ክሱ እውነት መሆኑ ቢረጋገጥ ምን አይነት ውሳኔ ወይም ቅጣት ይወሰናል?